# ትግላችን

ኣለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፣
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር፣ 3
ጥር 1966

ርሀብ በኢትዮጵያ::

## የአንዱ አሰቃቂ ወንጀል ታሪክ

በያዝነው ወር በአውሮጳ የሚወጡ ብዙ ጋዜጦች ኢት. በገባው ርሀብ በትንሹ ከሁለት መቶ ሺህ ሰው በላይ ማለቁን ይናገራሉ::በቀርጡ "ለሞንዴ" የተባለው በመላ ዓለም ተደማጭነት ያለው ጋዜጣ ወደ ኢት. ልዩ መልእክተኛ ልኮ ነበር:: ስለዚህም ሶስት ቀን በማከታተል ኢት. ስለገባው ጽኑ ርሀብ ሰፊ ሀተታ አቅርቧል::/ለሞንዴ ከ16እስከ18/1/74/ ይህ ጋዜጣ በጊዜው ያለው ሁኔታ እጅግ አሰቃቂ መሆኑን ካስረዳ በኋላ፣ለመርዳት የሚፈልጉት ግለሰቦችና ድርጅቶች ከመንግሥቱ ወኪሎች በኩል የሚደርስባቸውን ልዩ ልዩ እንቅፋቶች አየዘረዘረ አረመኔውን የኢት. መንግሥት በዓለም ፊት አጋልጧል::ከዚህም በማከታተል ይህ ሁሉ መከራ የደረሰው በድርቀት ምክንያት ብቻ ሳይሆን በመንግሥቱ ሰወች ቸልተኝነት፣ ግብዝነትና፣ መጠን የሳተ ስግብግብነት መሆኑን በግልጽ አስረድቷል::እንደዚሁም ይኢት. ህዝብ ችግር በጠቀላላው ከአገዛዙ መሆኑን ለማሳየት ይህን የይሁዳ አንበሳ°ስዕልለአንባቢወቹ



(Dessin de Bonnaffé.)

አቀርቧል::በመጨረሻም የኢት. ችግር ሊፈታ የሚችለው የመሬት ድልድል በሚገባ ሲከናወን መሆኑን አበሰር ይህንን ደግሞ ባላባቶቹ ከራሱ ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ/የንጉሶቹ ንጉሥ የሚባለው ሰው በያዘው መሬት ሲታሰብ የባላባቶቹም ባላባት"ነውና/በጥብቅ የሚቃወሙ መሆናቸውን አስረድቷል::

የሆነ ሆኖ ይህ ሁሉ ሰው እያለቀ አረመኔው መንግሥት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ "አሁን ሁኔታው ተረጋግቷል" እያለ ማሳገጥ ጀምሯል:: ግን "ሁኔታው የተረጋጋው"እንዴት ነው:: ርሀብ ከሀገራችን ገጽ ጠፋ ወይ::ወይስ ለወደፊቱ የሚጠፋበት ተዐምር ተገኝቶ ይሆን::አይደለም::በዚህ ጉዳይ ላይ ለዚህ ጋዜጠኛ ደሴ የሚገኝ አንድ አገር ወዳድ ሀኪም እንደህ ብሎ ነግሮታል:: "ሁኔታው የተረጋጋው መዘለቅ ያልቻሉት ሁሉ ሞተው ስላለቁ ብቻ ነው::"አወን ሩብ ሚልዮን ወገኖቻችን ሶስት ዓመት ሙሉ ማንም ሳይደርስላቸው የተናነቁት ከፋ ቀን አሸንፏቸው አልቀዋል:: ይህንን እያዩ "አሁን ሁኔታው ተረጋግቷል" እያሉ በህዝብ ስቃይ ማሳገጥ የአረመኔዎችን ልበ ደንዳናነት የሚጠይቅ ወንጀል ነው::

ደግሞስ "ችረጋጋ"ይባላል እንጅ የወገኖቻችን መከራ ገና መች አለቀ::መከራቸው ትላንት አልጀመረም:: ቢያንስ ሶስት ዓመት ያንገላታቸው ጽኑ ርሀብ ነው:: ዛሬ ለቀን መገፊያ ቁራሽ እንጀራ አገኙና ችግራቸው ተፈጸመ ማለት አይደለም::ነገስ::የሀገሪቱን የመሬት ስሪት ግፈኛነት፣የመንግሥቱን አረመኔነት፣ የነኃይለሥላሴን ግብዝነትና ስግብግብነት የሚያውቁ ሁሉ በዚህ "ነገስ"በሚለው ጥያቄ በመጨነቅ ላይ ናቸው::ለዚህ"ለሞንዱ"ጋዜጠኛ ደሴ ለእርዳታ የሄደ አንድ ሚሲዮናዊ ያቀቆት ይህንኑ ጭንቀታቸውን ነው:: እንደህ ይሉታል::"አወን:: እነዚህን ሰዎች ከርሀብ አስጥለናቸው ጥሩ ነው::ነገስ::ከነገ ወዲያስ::እና አገሩን ለቀን



ስንሄድ::" በዚሁ ላይ ደግሞ አንድ ኢትዮጵያዊ ሀኪም "ስለነገ"ሲያወራው እንደህ እንዳለው ጽፏል:: "ቢበዛ ተበፋችን እነዚህን ወገኖቻችንን ቀድሞ የነበሩበት ሁኔታ መመለስ ብቻ ነው::"

እዚህ ላይ "የቀድሞው ሁኔታ ምንድን ነበር::"ይላል ጋዜጠኛው በመገረም ራሱን እየጠየቀ::ወዲያው ደግሞ በማከታተል በጠቅላላው የኢትዮጵያን ህዝብ ሁኔታ ለአንባቢዎቹ ይገልጻል:: "የቀድሞው ሁኔታ በሚልዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እጅግ አጠራጣሪ በሆነው በማጣትና በርሀብ በማለቅ ጠርዝ ላይ ተንጠልጥለው ቀናቸውን የሚገፉበት ኑሮ ነበር:: አንድ ኢትዮጵያዊ በነፍስ ወከፍ በዓመት የሚያገኘው ገቢ 60 ብር ሲሆን ይህ ገቢ ከህንድ አገር እንኳን ዝቅ ያለ ነው::ይህም ማለት የኢት. ህዝብ በዓለም ችግርና መጉሳቆል ካጠቃቸው ህዝቦች አንዱ ነው ማለት ነው::"

ይህንንም በኑሮ ጠርዝ ላይ የተንጠለጠለ ፊትና በተጨባጭ መልኩ ለማስረዳት በወሎና በትግራይ ያነጋገራቸውን ገበሬወች ታሪክ ለአንባቢወች አቀርቧል:: ከነዚህም ውስጥ አቶ አካሉ ይመር ከዋድላ፣ ባለፈት ሶስት ዓመታት ቤተሰባቸውን ለማዳን እንዴት ከርሀብ ጋር እንደተናነቁ፣እንዴት እንደተረቱ፣እንዴትስ ቤታቸው እንደተፈታ እንጀት የሚበላ ታሪካቸውን እንደህ እያሉ አዋይተውታል::

"ዝናብ ከጣለ ሶስት ዓመቱ ነው::በ1963 ዓም አዝመራ አልያዘም ነበር::በ1964 ዓም ለዘር ያስቀመጥነውን በልተን ቢያልቅብን ከሞት ለመትረፍ ስንል እህል መበደር ሆነብን::በጥር 1965 ዓም የጠበቅነው ዝናብ ቀረ:: የምንሆነው ጨነቀን::በበኩሌ ሁለት ኩርማን መሬት ነበረችኝ:: አንደኛዋን ሁለት አቅማዳ ጤፍ ለመበደር በወለድ አገድ ሰጠኋት:: መከፈል ተስኖኝ ከመሬቴ ተነቀልሁ::ትንሽ ቀን ቢገፋልን ብየ

ሁለተኛዋን ኮርማን መሬቴን በአስር ብር ሸጥኳት:: ሰኔና ሀምሌን ባደ እጄን ነኝ:: ግራ ቢገባኝ ሚስቴንና ሁለት ልጆቼን ዋድላ ትቼ ሥራም የሚቀመስም ፍለጋ አገር ለቀቄ ወጣሁ:: ወንድሜ ጋር ተያይዘን በአራት ቀናችን ደሴ ገባን:: ሥራም የሚቀመስም ጠፋ::እዛው ሆኜ ሚስቴንና ሁለቱንም ልጆቼን ተረዳሁ::"

ይህ ታሪክ የአቶ አካሌ ደመር ታሪክ ብቻ አይደለም:: በመላ የትግራይና የወሎ ዱሀ ገበሬዎች ባለፉት ሰባት ዓመታት መውጫው ጠፍቷቸው ሲፍጨረጨሩበት የነበረው አስቃቂ አዙሪት ነው:: ይኸው ጋዜጣ ለአንባቢዎቹ የሚያረጋግጥላቸው ይህንኑ አስቃቂ ዕውነት ነው::እንዲህ ይላል: "በደፈን ወሎ ይኸው ታሪክ ሸህ ጊዜ እየተደጋገመ ይሰማል::ሁልጊዜም ያው ነው:: አባትየው ሰባት ዓመት ሙሉ እየጨከነ ከሚሄደው ርሀብ ጋር ቤተሰቡን ለማትረፍ ይተናነቃል::ይዋትታል::ይፍጨረጨራል:: ይበደራል::ከብቱን ይሸጣል::መሬቱ የሱ ከሆነ መሬቱን ይሸጣል::መጨረሻም ይሸነፍና ቤቱን ፈቶ ቤተሰቡን ትቶ ብቻውን መንገድ ይጀምራል::ከሚዋትትበት ቀንቶት ወደ ወገኖቹ ለመመለስ እንኳን ሲያስብ ትቷቸው የሄደው ቤተሰቦቹ ማለቃቸውን ይሰማል"

"እንግዲህ እንደዚህ በደላቸውን ለዓለም ለመጮህ የበቁትና የተረፉት ከዚህ ረኸም ፈተና ተፍጨርጭረው በማምለጥ ወደ ከተማ የደረሱት ጥቂቶች ብቻ ናቸው::ደካሞቹ፣ በተለይ ደግሞ ሽማግሌቸና ህጻናት አስቀድመው አልቀዋል:: አንዱ ጋዜጠኛ ባለፈው ወር ሲጽፍ "በአንዳንድ መንደሮች ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት አይታዩም:: በሙሉ አልቀዋልና::" ያለው ለዚህ ነው:: የተረፉት ጥቂት ወገኖቻችን እንዲህ ታሪካቸውን አሰሙን::ትተዋቸው የመጡት መንደሮቻቸውስ:: ያለቁት ሚስቶቻቸውስ::ሽማግሌዎቻቸውስ::ልጆቻቸውስ:: የነሱን ታሪክ በእርግጥ የሚያውቅ ማንም የለም::ቢሆንም ይኸው ጋዜጠኛ ስለ



እነሱም የታዘበውን ለታሪክ አስፍሮታል:: እንዲህ ይላል::

"ከአውራ ጎዳናው አንዱ ቀን ያህል በእግር ከተገባ ትኩስ መቃብሮች በሽህ ይቆጠራሉ::በያለበት እሱው ነው:: በትግራይና በወሎ በአንዳንዱ መንደሮች በጥዱፊያ የተካሱ መቃብሮች ለቁጥርም ያስቸግራሉ:: እንዲያውም በአንዳንዱመንደሮች ሰው ሁሉ ጎጆውን እየፈታ አገር ለቀ ሄዱዋል:: የቀረት መቃብሮች ብቻ ናቸው::...... የወሎ ተራሮች በያለበት በትኩስ መቃብሮች ተበርብረው ይታያሉ::"

አወን:: በገፍ የረገፉት ወገኖቻችን በደላቸውን የማሰማት ወግ እንኳን አልደረሳቸውም::ታሪካቸውን አላወራንም:: ግን "በትኩስ መቃብሮች የተበረበሩት" የወሎ ተራሮች ለናም ሆነ ለመጭው ትውልድ በኃይለስላሴና በሊት. ፊውዳል ሥርዐት በወገኖቻችን ላይ ለተፈጸመባቸው ወንጀል ምንጊዜም "አቤት" እንዳሉላቸው ይኖራሉ::

አንዱ ህዝብ እንደዚህ በስቃይ እየተጠበሰ ሲፈተን የሥርዐቱ ግፈኝነት፣የመንግሥቱ ጭካኔ፣ የሃላፊዎቹ ቸልተኝነት ፈጽሞ እንግዳ ነገር የሆነበት ይህ ጋዜጣ ትግራይና ወሎን ተመልክቶ አዴስ አበባ ተመለሰ:: ባየው ሁሉ እጅግ አርጉ መደነቁን ሲያወራ የአረመኔዎቹ የገንዘብ ሚኒስትር "ምሁሩ" አቶ ማሞ ታደሰ እንዲህ አያለ መለሰልኝ ይላል::

"አይደንቀኝም:: እናንተ እኮ ይህ ሁሉ እንግዳ ነገር የሚሆንባችሁ በምዕራባውያን ዓይናችሁ እያያችሁት ነው::"

እናንተስ "ምሁሩ" ማሞ ታደሰ:: እናንተስ እነዚህ ሁሉ ወገኖቻችን እንደዚህ ሰባት ዓመት ሙሉ ከርሀብ ጋር ሲተናነቁ ቀስ በቀስ ሲሸነፉ፣ንብረታቸው ሲበተን፣ ቤታቸው ሲፈታ፣በኋላም እንደዝንብ ሲረግፉ አስቻላችሁ ዝም ያላችኋቸው በምን ዓይናችሁ ተመልክታችኋቸው ነው::ከፋ ቀን ገብቶ እናትና ልጅ

ቁራሽ እንጀራ እየተናጠቁ ሲላቀሱ፣ ተራሮቻችን 'በትኩስ መቃብሮች ሲቦረቦሩ፣' የግል ጥቅማችሁና ግብዝነታችሁ አሸንፏችሁ ርሀቡን የሸሸጋችሁን የነዚህን ወገኖቻችንን ስቃይ በምን ዓይን አይታችሁት ይሆን:: ደግሞስ በኋላ ስትጋለጡ የኢት. ህዝብ ሳይተርፈው ያካፈለውን ገንዘብ፣ የዓለም ህዝብ የላከላቸውን እህል ሸጣችሁ የበላችሁባቸው መከራቸውን በምን ዓይን እየመዘናችሁት ኖርዋል::

በኢትዮጵያዊ ዓይናችን እንዳትሉን:: ኢትዮጵያውያኖቹማ ባይተርፋቸው ከሚበሉት ቆርሰው አካፈሉ:: ኢትዮጵያውያኖቹማ ቀናንሳችሁ ከምትከፍሏቸው የለፋታቸው ዋጋ እንደገና ቀንሰው ለተራበው ወገናቸው አካፈሉት:: ኢትዮጵያውያኖቹማ እናንተን የቀን ጅቦችን እናምን ብለው ሳይተርፋቸው የሰበሰቡትን እዚው ድረስ ወስደው ለወገናቸው አካፈሉ:: ኢትዮጵያውያኖቹማ በውጭ አገር የእናንተን አጉል መመጻደቅ ሰባበረው መላው ዓለም አፍናችሁ ለምትጨርሱት ወገናቸው እንዲደርስ ከዳር እስከ ዳር በመጮኽ እርዳታ ጠየቁ::

'ምሁሩ'ማሞ ግፍ ሲያዩ መጮህ ለነጮች ብቻ ከሰማይ የወረደ ጸጋ መስሎህ ይሆን:: ኢትዮጵያን በመሰለች ሀብታም አገር እፍኝ የማትሞሉ ጥቂቶች እየተትረፈረፋችሁ ራብ ሚሊዮን ወገኖቻችን ሲያልቁ እኛም 'የምዕራባውያን ዓይን' የሌለን 'እንግዳ ነገር ሆኖብናል' እነዚህን በኢት. ህዝብ ላይ የምትፈጽሙትን ዓይን የሚያወጡ ግፎች ለማየት የግድ ነጭ ሆኖ መወለድ አያስፈልግም:: እርግጥ ጉዳቹንና ግፋችሁን መላው ዓለም ሲያየው እናንተ አልታያችሁ ይሆናል:: ግን እንዲህ የሆነበት ምክንያት ግብዝነታችሁና ስግብግብነታችሁ ጭራሹን ከሰውነት መስመር ስላስወጣችሁ ነው እንጂ 'በምዕራባውያን ዓይን ስላልታያችሁ' አይደለም::



አወን:: አሁን ሁኔታው 'ተረጋግቷል' ይባላል:: እንዲያውም በየከተማው የፈሰሱት ድሀ ገበሬዎች የሰው እጅ እያዩ መትረፍም ከቁም ነገር ተቆጥሮባቸው 'ወደ መጡበት እንዲመለሱ' በአረመኔው መንግሥት በመታዘዝ ላይ ናቸው:: እንዲያውም ለዚሁ ጋዜጠኛ አንዱ ሚኒስትር እንዲህ ብሎ እንዳጫወተው ጽፏል:: 'ሰወቹ ሥራ ፈተው ቁጭ ብሎ መበላትን እየለመዱ ሄደዋል:: ይህ ስንፍናን ያመጣል::' ስለታታሪው የኢት. ገበሬ 'ስንፍና' እዚህ ላይ ከነዚህ ግብዞች ጋር አፍ መካፈት አንፈልግም:: ለነገሩ ግን እማን ላይ ቆመሽ እግዜርን ታሚያለሽ የሚለውን የአባቶች ተረት አስታውሰናቸው እናልፋለን:: የሚጨንቀን እነዚህ ገበሬዎች 'ወደ መጣችሁበት ተመለሱ' ሲባሉ ነው::

አባወራው ሚስትና ልጆችን ቀብሮ፣ እናት ከልጆቿ እህት ከወንድሟ፣ ወንድም ከወንድሙ፣ ተነጣጥለዋል:: ቤተሰብ ተበትኗል:: የወሎና የትግራይ መንደሮች በሚወዷቸው ወገኖቻቸው 'ትኩስ መቃብር ተቦርቡረዋል' በዚህ መልክ ገና ሞት ሞት የሚሸቱ መንደሮቻቸው ምን አለን ብለው ይመለሱ:: ለኑሮዋቸውስ ማረጋገጫ ምን ይዘው ይመለሱ:: እንደዚህስ ተመለሱ ስትሏቸው እንደገና ደግሞ የኢት. ህዝብ ሳይሰማ፣ የዓለም ህዝብ ሳይጠረጥር በዚያቸው በመንደራቸው ዓለም ታፍነው ሶስት ዓመት እንደገና ከርሀብ እንዳይተናነቁ እንደገና ተሸንፈው ቤታቸው እንዳይፈታ፣ እንደገና የትግራይና የወሎ ተራሮችና መንደሮች 'በትኩስ መቃብሮች እንዳይቦረቦሩ' ምን ዋስትና ትሰጧቸዋላችሁ:: ምንም ልትሰጧቸው አትችሉም::

ዘር ትሰጧቸዋላችሁ ወይ:: ማረሻ ትሰጧቸዋላችሁ ወይ:: ለማረሻ በሬዎች፣ ለዘር፣ ለሌላም ለመቋቋሚያቸው እስቦ የዓለም ህዝብ የላከላቸውን ገንዘብ ሳትሰርቁ ትሰጧቸዋላችሁ ወይ:: መሬቱን እዚህ ግባ በማይባል ዋጋ ለተቀማው ገበሬ የሚ

ያርሰበት ሌላ መሬት አዘጋጅታችሁላታል ወይ:: ቢሰኖው አዝመራ አልይዝ ሲለው ከልጁ አፍ እየነጠቀ ለባለመሬቱ እንዲያስረክብ የሚያዘውን ደንብና ህግ አስቀርታችሁላታል ወይ::ይህን ሁሉ አላረጋገጣችሁለትም::

ለታረጋግጡለትም አትችሉም:: ምክንያቱም ዘራፊዎች እናንተው ስለሆናችሁ ዘረፋን ለታጠፉ አትችሉም:: የኢት. ህዝብ ችግር ሁሉ በመሰረቱ ከናንተ ወግና ስርዐት ጋር የተያያዘ ነገር ነው:: ስለዚህ እናንተ ባትጠፉ ምንም ዓይነት ቋሚ መፍትሄ ሊገኝ አይችልም::

ዛሬ በአጣዳፊ ችግር ላይ የሚገኙት ወገኖቻችን ዘር፣ ማረሻና መቋቋሚያ እንደሰጧቸው አገር ወዳድ የሆነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የአረመኔዎቹን መንግሥት ወጥሮ መያዝ ተግባሩ ነው:: ነገር ግን ይህ በምንም አይነት ዘላቂ መፍትሄ ሊሆን እንደማይችል ግለጽ መሆን አለበት::ዘላቂው መፍትሄ የሚገኘው መሬቱን ለህዝቡ የሚያደላድልና በጠቅላላው ለጥቂቶች ባይሆን ለመላው ህዝብ ጥቅም የቆመ መንግሥት ሲመጣ ብቻ ነው:: ይህም ህዝባዊ መንግሥት ሊመጣ የሚችለው በፊውዳሊዝምና በኢምፒርያሊዝም መቃብር ላይ ስለሆነ ለዚህ ረጅም ትግል መሰለፍም አለብን::

# ይዘት


1. ርዕሰ አንቀጽ ገጽ 1
2. ረሃብ በኢትዮጵያ 5
3. የዓለም ጋዜጦች የኢትዮጵያን መንግሥት ያወግዛሉ 13
4. የሰብአዊ መብት ዶምፀ 15
5. ለዲሞክራሲና ለፍትህ ለሚታገሉ የተደረገ ጥሪ 18
6. የጊኒ ቢሳዎ ህዝባዊ ትግል 20
7. የመንግሥቱን ጋዜጦች ስናገላብጥ 31
   “ኃይለ ሥላሴና የኢትዮጵያ ፍርኛ”
8. የትግላችን ትርጉም “የመቀሃዬ ዘመቻ” 46
9. ይድረስ ለትግላችን 56
10. ኢትዮጵያ በዓለም ጋዜጦች 58
   “የኢትዮጵያ መንግሥት ለፖርቱጋል ይሰልላል”

ሾካ፡ “መንገደኛ” 62